ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ Ginbot 7 Movement for Justice Freedom and Democracy

# ሕወሓትና በትግርኛ ተናጋሪዎች ሙሉ ቁጥጥር ስር የወደቀዉ መከላከያ ሠራዊት ከአራት አመታት በኋላ በድጋሚ ሲፈተሽ

**መስከረም 2007 ዓ.ም**

ሕዝባዊ ሓርነት ወያኔ ትግራይ (ሕወሓት) ምን ያክል የኢትዮጵያን የፖለቲካ መዋቅሮች እንደሚቆጣጠር ለማወቅ በአገሪቱ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ተቋሞች ዉስጥ ዋና ዋና የትዕዛዝ ሰጪና ቁጥጥር ቦታዎች ላይ በሀላፊነት የተቀመጡትን የትግራይ ተወላጆች ብዛት መመልከቱ በቂ ይመስለናል። የሕወሓት መሪዎች ስልጣን በያዙባቸዉ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት ዉስጥ እየገነቡት ላይ ያለዉን ስርዐት መልካምና ሁሉን አቀፍ ስርዓት ለማስመሰል አንዳንድ ከነርሱ ቁጥጥር ዉጭ መተንፈስ እንኳን የማይችሉ የሌላ ብሄረሰብ ተወላጆችን አልፎ አልፎ ስልጣን ላይ አስቀምጠዋቸዉ ነበር። ዛሬ ሕወሓቶችን እራሳቸዉን እጅግ በጣም በሚያሳፍር መልኩ እነዚህ በጥንቃቄ ለቅመዉ ያመጧቸዉንም የሌላ ብሄረሰብ ተወላጆች ወደመጡበት መልሰዋቸዉ በሁሉም መስክ ቁልፍ የሆኑ የአገሪቱን የስልጣን ቦታዎችን የሚቆጣጠረዉ የትግራይ ተወላጅ ሕወሓቶች ብቻ ሆነዋል። አያሌ ኢትዮጵያዉያን የህወሓትን አገዛዝ "ዘረኛ" አገዛዝ ነዉ ብለዉ የሚጠሩት ይህንን ሙልጭ ያለ በዘር ላይ የተመሰረተ ጭፍን አገዛዝ ተመልክተዉ ይመስለናል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ ለፈጠረዉ ዘረኛ ስርዓት ብቸኛ ምሳሌ ሆኖ መቅረብ የሚችለዉ ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ ነጮች የፈጠሩት ዘረኛ (Apartheid) ስርዓት ብቻ ነዉ። በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ በተለይ በቁጥሩ ከፍተኛ ብልጫ ያለዉና ትግርኛ ተናጋሪ ያልሆነዉ ሠራዊት እጅግ ያኮረፈ፤ የተቆጣና ያመረረ ሠራዊት ከመሆኑ የተነሳ እራሱን የሚመለከተዉ እንደ አገር መከላከያ ሠራዊት አባል ሳይሆን እንደ ህወሓት የቤት ዉስጥ አገልጋይ ባሪያ ነዉ። ይህ የሕወሓት ዘረኞች በሠራዊቱ ላይ የፈጠሩት የመገዛትና የበታችነት ስሜት በየቀኑ ከፍተኛ ቁጣና የዉስጥ ለዉስጥ ተቃዉሞ የሚገጥመዉ ቢሆንም ህወሓት በዘረጋዉ ከፍተኛ የአፈና መረብ የተነሳ የህዝብ መነጋገሪያ አርዕስት መሆን አልቻለም። የህወሓት መሪዎችም ቢሆኑ ይህንን ቁጣና ተቃዉሞ በሚገባ ስለሚያዉቁ "ግምገማ" እያሉ በሚያዘጋጁቸዉ መድረኮች ላይ እንደዚህ አይነቶቹን በእነሱ የበላይነት ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን ማስተናገድ ቀርቶ ጥያቄዎቹ እንዲነሱም አይፈቅዱም። አንዳንዴ ደፍረዉ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሱ ግለሰቦች ሽብርተኛ፣ የደርግ ስርዐት ናፋቂዎች፣ ጠባብ ብሄረተኞች ወይም የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች የሚል ተቀጽላ ስም ይሰጣቸዋል። ዛሬ የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸዉ በተለያዩ የወያኔ እስር ቤቶች ዉስጥ የሚሰቃዩት ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ለዚህ አሳዛኝ ሁኔታ የበቁት በመከላከያ ተቋሞች ዉስጥ ሠራዊቱን በየትኛዉም እርከን የሚመሩ መኮንኖች አመዳደብ ወታደራዊ አመራር ችሎታን፤ ልምድንና የብሄር ስብጥርን ያካተተ መሆን አለበት ብለዉ ደፍረዉ በመናገራቸዉ ነዉ።

ዛሬ የወያኔን መከላከያ ሠራዊት እየለቀቁ ከአገር የሚወጡ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል። እነዚህ ወታደራዊ መሪዎች፤ የበታች መኮንኖች፤ ባለሌላ ማዕረጎችችና ተራ ወታደሮች ከጠላት እንከላከላን

ብለዉ የማሉላትን እናት አገራቸዉን እየለቀቁ የሚወጡት በወያኔ ጦር ዉስጥ ስር የሰደደዉ ዘረኝነትና በዚህ ዘረኝነት ላይ የተመሰረተዉ አመራር የሚያደርስባቸዉ በደል አንገፍግፏቸዉ ነዉ። በየጎረቤቱ አገር ተሰድደዉ በችግር ላይ የሚገኙ ምርጥ የኢትዮጵያ የወታደራዊ ሳይንስ አዋቂዎች ሁሉም በአንድ ድምፅ የሚናገሩት ሠራዊቱ ዉስጥ ይደርስባቸዉ የነበረዉ ንቀትና ዉርደት የሰዉ ልጅ መሸከም ከሚችለዉ በላይ መሆኑን ነዉ።

ሕወሓትን ለረጂም ግዜ የመራዉ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ሥልጣን በያዙባቸዉ በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት አመታት ጊዜያት ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች ሰዎች መያዛቸዉን አስመልክተዉ ሲናገሩ ህወሓት ለ17 አመታት የደርግን አምባገነናዊ ስርዓት ሲዋጋ የፈጠረዉ ወታደራዊና ድርጅታዊ ግዝፈት አብዛኛዉ የወታደራዊና የደህንነት አመራር ቦታ በህወሓት ታጋዮች እንዲያዝ ምክንያት ሆኗል ብለዉ ከተናገሩ በኋላ ይህ አሰራር በሂደት ሙሉ በሙሉ እንደሚቀይርና የኢትዮጵያ የፖለቲካና ወታደራዊ የሥልጣን ክፍፍል የአገሪቱን ብሄር ብሄረሰቦች ጥንቅር ያገናዘበ ይሆናል ብለዉ ተናግረዉ ነበር። ሆኖም ዛሬ ይህ ከተነገረ ከሃያ አመታት በኋላና ይህንን የተናገረዉ መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት ከተለየ ከሁለት አመታት በኋላ የሕወሓት የሥልጣን ቁጥጥር ጭራሽ አጋሽቦ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከትግርኛ ቋንቋ ዉጭ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ወደ ሥልጣን አይመጡም የሚባልባት አገር ሆናለች። በኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ በገነባዉ መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ የዕዝ፤ የክፍለጦርና የመምሪያዎች አዛዥ ለመሆን ዋነኛዉ መለኪያ የትግራይ ብሄረሰብ ተወላጅና የሕወሓት ታማኝ አገልጋይ መሆን ነዉ እንጂ ችሎታ፤ ልምድ፤ ብቃትና የወታደራዊ ሳይንስ ክህሎት አይደለም። ችሎታ፤ ልምድና ብቃት መመዘኛ ሆነዉ የሚቀርቡት በመጀመሪያ ለሹመት የታጨዉ መኮንን የትግራይ ተወላጅ እና የሕወሓት ታማኝ አገልጋይ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ብቻ ነዉ።

የሕወሓት የስልጣን ሞኖፖሊ በወታደራዊ ደህንነት ተቋሞች ላይ ብቻ ተወስኖ አያበቃም። አብዛኛዉን የአገሪቱ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ተቋሞችም ወይ ከላይ አለዚያም ከታች ሆነዉ የሚቆጣጠሩት የሕወሓት ታማኝ አገልጋይ ትግርኛ ተናጋሪዎች ናቸዉ። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለይስሙላ የተቀመጠና ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የመጡ ሰዎች የሚገኙበት አገዛዝ አለ፤ በዚህ አገዛዝ ዉስጥ ደግሞ አገሪቱን ወዳሰኘዉ አቅጣጫ በዘፈቀደ የሚዘዉረዉና ከትግርኛ ተናጋሪዎች ዉጭ ሌሎች የማይገኙበት በአገዛዙ ዉስጥ ሌላ ቡድናዊ አገዛዝ አለ። ዛሬ እነ ኃ/ማርያም ደሳለኝ፤ አባዱላ ገመዳና ደመቀ መኮንንን የመሳሰሉ ምስለኔዎች ስልጣን ላይ የተቀመጡ ነገር ግን የሕወሓት ጌቶቻቸዉ ከሚነግሯቸዉ ዉጭ በራሳቸዉ ምንም አይነት ትዕዛዝ መስጠት የማይችሉ አሻንጉሊቶች መሆናቸዉን እነሱ አራሳቸዉም የተገነዘቡት ይመስላል።

ግንቦት ሰባት- የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የዛሬ አራት አመት (እ.ኤ.አ.በ2009) በዘር የተደራጀዉን የወያኔ መከላከያ ተቋም አደረጃጀት ምን እንደሚመስል በመረጃ አስደግፎ ለአለም ህዝብ ማቅረቡ የሚታወስ ነዉ። ግንቦት ሰባት ይህ ይሻሻላል ወይም አደረጃጀቱ በሂደት ይለወጣል ተብሎ የተነገረለት የወያኔ መከላከያ ተቋም ጭራሽ ከድጡ ወደማጡ እያዘገመ መሆኑን በጥናታዊ መረጃዎች አስደግፎ እንደሚከተለዉ ያቀርባል። በዚህ ጥናት ዉስጥ የወያኔን መከላከያ ሠራዊት ይዘትና ቅርጽ በሚገባ የሚያዉቁ፤ ሠራዊቱን ለቅቀዉ የወጡና አሁንም በሠራዊቱ ዉስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ ከፍተኛ መኮንኖች ተሳትፈዋል። ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበዉ ሠንጠረዥ የተለያዩ የመከላከያ ተቋም የስልጣን ቦታዎችን፣ በስልጣን ቦታዎችን እነ ማን እንደተቀመጡና የተወለዱበትን ብሄረሰብም ጭምር ያሳያል።

| Military Ranks | Tigrie | Amhara | Oromo | Agew | SNNPR | Mixed | Total position |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| National level: Highest Rank Command Chiefs | 9 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 10 |
| Heads of Army Commands(Six Cores) | 4 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 5 |
| Heads of Army Command Divisions | 13 | 3 | 4 | 1 | 0 | 1 | 22 |
| HQ Combat Service & Combat Support Staff Commanders | 13 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 14 |
| Military Training Center Commanders | 10 | 0 | 2 | 1 | 0 | 0 | 13 |
| **Total Number of Generals** | **49** | **4** | **8** | **2** | **0** | **1** | **64** |



| ከፍተኛ ወታደራዊ ዕዝና ቁጥጥር ዘርፎች የበላይ ሀላፊዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| No | ሙሉ ስም | የሀላፊነት ቦታ | ማዕረግ | ብሄር |
| 1 | ሳሞራ የኑስ | የጦር ኃይሎች ኤታማጆር ሹም | ጄኔራል | ግማሽ ትግሬ |
| 2 | ሰአረ መኮንን | የስልጠና ሃላፊ | ሌፍቴናንት ጄኔራል | ትግሬ |
| 3 | ኢብራሂም አብዱጀሊል | የሎጊስቲክ ሃላፊ | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |
| 4 | ገብሬ ዴላ | በመከላከያ ሚኔስቴር ዉስጥ የደህንነት ሃለፊ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 5 | አበባዉ ታደሠ (በቅርቡ ከሰራዊቱ የተባረሩ) | የዘመቻ ሀላፊ | ሌፍቴናንት ጄኔራል | አገዉ |
| 6 | ብርሐኔ ነጋሽ | በመከላከያ ሚኒስቴር የመሰረተ ልማትና ኮንስትራክሺን ሃላፊ ሚኒስቴር ደኤታ | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |
| 7 | አደም መሐመድ | የአየር ኃይል አዛዥ | ሜጀር ጄኔራል | አማራ |
| 8 | ክንፈ ዳኘዉ | የመከላከያ እንዱስትሪ ዋና ዳይሬክተር | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 9 | ዮሐንስ ገ/ስቀል | የሰላም አስከባሪ ግዳጅ ኃይል ዋኛ አዛዥ | ሌፍቴናንት ጄኔራል | ትግሬ |
| 10 | መሐመድ ኢሻ | የልዩ ኃይል አዛዥ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |

| የዕዝ ሃላፊዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| No | ዕዝ | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ብሄር |
| 1 | ማዕከላዊ ዕዝ | ዮሐንስ ወልደ ጊዮርጊስ | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |
| 2 | ሰሜን ዕዝ | ገብራት አየለ | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |
| 3 | ምዕራብ ዕዝ | ብርሃኑ ጁላ | ሜጀር ጄኔራል | ኦሮሞ |
| 4 | ምስራቅ ዕዝ | አብርሃ ወልደ ማሪያም | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |
| 5 | ደቡብ ምስራቅ ዕዝ | ፍስሃ ኪዳኑ | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |

# የምድር ጦር - ክፍለ ጦር አዛዦች

## ማዕከላዊ ዕዝ

| No | ክፍለጦር | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ብሄር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 8ኛ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር | ጀማል መሐመድ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 2 | 31ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ተስፋይ ወልደ ማሪያም | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 3 | 35ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ምስጋናዉ አለሙ | ብርጋዴር ጀኔራል | አገዉ |
| 4 | 24ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | መሐመድ ተሰማ | ብርጋዴር ጀኔራል | አማራ |
| 5 | 22ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ገብረ እግዚአብሄር በየነ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 6 | 33ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | አመሃ ገብሩ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |

## ሰሜን ዕዝ

| No | ክፍለጦር | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ብሄር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 14ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | አብዱራህማን እስማኤል | ብርጋዴር ጀኔራል | ኦሮሞ |
| 2 | 21ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ዋኘው አማረ | ብርጋዴር ጀኔራል | አማራ |
| 3 | 11ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | አደምነህ መንግስቴ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 4 | 25ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ዜናዊ ገብረ እግዚአብሄር | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 5 | 22ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | በላይ ስዩም | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 6 | 4ኛ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር | ሂንቲሳ ወልደጊዮርጊስ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |

| ደቡብ ምስራቅ ዕዝ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| No | ክፍለጦር | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ብሄር |
| 1 | 19ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ጥጋቡ ይልማ | ብርጋዴር ጀኔራል | አማራ |
| 2 | 44ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | አብርሃ ተስፋዬ | ብርጋዴር ጀኔራል | ኦሮሞ |
| 3 | 13ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | የማነ ሙሉ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 4 | 12ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | | | |
| 5 | 32ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ከድር አራርሳ | ብርጋዴር ጀኔራል | ኦሮሞ |
| 6 | 6ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ወልደገብርኤል ባቢ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |

| ምዕራብ ዕዝ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| No | ክፍለጦር | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ብሄር |
| 1 | 23ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | አታክልቲ በርሄ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 2 | 43ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ሙላቱ ጀልዱ | ብርጋዴር ጀኔራል | ኦሮሞ |
| 3 | 26ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | ፍስሃ በየነ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 4 | 7ኛ ምድር ጦር ክፍለ ጦር | አስራት ዳመሮ | ብርጋዴር ጀኔራል | ድብልቅ |

# በመከላከያ ሚኒስቴር የዉግያ አገልግሎትና ድግፍ ሰጪ ተቋሞች ሀላፊዎች

| No | የመከላከያ ዘርፎችን ክፍሎች | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ብሄር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መከላከያ ልማትና ምርምር ክፍል | ገብረ ሜካኤል በየነ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 2 | መከላከያ መገናኛ ክፍል | ተካልኝ ከሳሁን | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 3 | መከላከያ ኢንዱስትሪ ክፍል | ክንፈ ዳኘዉ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 4 | መከላከያ ማስተማሪያና ማነጫ (Indoctrination) ማዕከል | ገብረ ኪዳን ገብረ ማሪያም | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 5 | መከላከያ ፍትህ አገልግሎት | አስካለ ብርሀን | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 6 | መከላከያ ሕዝብ ግንኙነት ክፍል | ደስታ አብቹ | ሜጀር ጀኔራል | ኦሮሞ |
| 7 | መከላከያ የመረጃ ደህንነት ክፍል | ተክለ ብርሀን ካህሳይ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 8 | መከላከያ አስተዳደር ዘርፍ | መሃሪ ዘዉዴ | ሜጀር ጀኔራል | ትግሬ |
| 9 | መከላከያ ገንዘብ ዘርፍ | ዘዉዱዋ ኪሮስ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 10 | መከላከያ ዕቃ ግዢ | ሙሉ ግርማይ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 11 | መከላከያ እንዱስትሪ አስተባበሪ | ወዲ ነጋሽ | ብርጋዴር ጀኔራል | ትግሬ |
| 12 | መከላከያ አስተዳደር፣ ጸጥታና ደህንነት ክፍል | ወዲ ተዊቅ | ኮሎኒል | ትግሬ |
| 13 | መከላከያ የቁጥጥር ማዕከል | ዘዉዱ በላይ | ብርጋዴር ጀኔራል | አማራ |
| 14 | መከላከያ በጀት መምሪያ | ብርሀኔ አበራ ፣ ሚኒስትር ዴኤታ | ሲቪል | ትግሬ |
| 15 | የመከላከያ ሰላም አስጠባቂ አስተባባሪ | ሃሰን ኢብራሀም | ሜጀር ጀኔራል | አማራ |

| ወታደራዊ ማሰልጠኛ ጣቢያ አዛዦች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| **No** | **መከላከያ የማሰልጠኛ ጣቢያዎች** | **ሙሉ ስም** | **ማዕረግ** | **ብሄር** |
| 1 | የትዕዛዝ ዕዝና ሰዉ ኃይል ማሰልጠኛ ማዕጀል | ጂጂ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 2 | ሀየሎም አርአያ አካዳሚ | ነጋሽ ህሉፍ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 3 | ሁርሶ እግረኛ ጦር ማሰልጠኛ ማዕከል | ኩሜራ ነገሬ | ብርጋዴር ጄኔራል | ኦሮሞ |
| 4 | አዋሽ አርባ ሜካናይዝድ ሚሊቴሪ ማሰልጠኛ ማዕከል | ሙዜይ መኮንን | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 5 | ብላቴ ልዩ ወታደራዊ ኃይል ማሰልጠኛ ማዕከል | አብርሃ ተስፋዬ | ኮሎኔል | ትግሬ |
| 6 | መከላከያ ምህንድስና ኮሌጅ | ሀለፎም እጅጉ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 7 | ሚሊታሪ የጤና ሳይንስ አካዳሚ | ተስፋይ ግደይ | ሜጀር ጄኔራል | ትግሬ |
| 8 | ሙሉጌታ ቡሊ የቴክኒክ ማሰልጠኛ ኮሌጅ | ሙሉዬ አማረ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 9 | መከላከያ ሎጂስቲክ ኮሌጅ | ያይኔ ስዩም | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 10 | መከላከያ ደህንነት ኮሌጅ | ጉዕሽ ጽጌ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 11 | መከላከያ ግብት ማነጅመንት ኮሌጅ | ዲሪባ መኮንን | ብርጋዴር ጄኔራል | ኦሮሞ |
| 12 | ብር ሸለቆ ወታደራዊ ማሰልጠኛ | ሳለህ በሪሁ | ብርጋዴር ጄኔራል | ትግሬ |
| 13 | መቀሌ ህብረት የሚለታሪ አካዳሚ | ይመር መኮንን | ብርጋዴር ጄኔራል | አገው |
| | | | | |